**ሳምንታዊ ዜና (ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የወያኔው መሪ መለስ ሚስት አዜብ መስፈን ከአፈ ጉባኤ ተሾመ ቶጋ ጋር ግጭት ፈጠሩ፣ የአንበሳ ከተማ አውቶቡስ ድርጅት ሠራተኞችን በመዋቅር ሰበብ ሊያባርር ነው፣ የአገዛዙ የእስር ቤት ፖሊሶች የፖለቲካ ትምህርት ሊሰጣቸው ወደ ካምፕ ገቡ፣ ሕዝቡ በተራበበት ወቅት አገዛዙ በ130 ሚሊዮን ብር ለፓርቲው ሕንፃ ሊያሰራ መሆኑ ተጋለጠ፣ ከ10 ዓመት በፊት በታተሙ ጋዜጦች ላይ አሳታሚና አዘጋጆች በፖሊስ እየታደኑ ነው፣ ህትመት ካቆመ 8 ዓመቱ የሆነው ጋዜጣ ዘጋቢ የነበሩና ከሞቱ 5 ዓመት የሆናቸው ሰው ተከሰው በፖሊስ እየተፈለጉ ነው »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ..................................**

የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤና የወያኔ ካድሬ የሆነው ተሾመ ቶጋ እና ሁሉም ቦታ አለሁ አለሁ የምትለው የመለስ ዜናዊ ሚስት እርስ በእርስ መሻኮት መጀመራቸውን የምክር ቤት ውስጥ አዋቂ መንጮች ገለፁ::

ሁሉን ሥልጣን ከባሏ ቀጥሎ ለመጠቅለል እየተሯሯጠች ያለችው አዜብ መስፍን ለኢትዮጵያ በኤድስ ስም የሚመጣውን ገንዘብ የምትቀበለው እሷ በመሆኗ እንደልቧ በፈለገችው መንገድ እየመነዘረች መሆኑን የገለፁት ምንጮች በቅርቡ በዚሁ ዙሪያ ለመወያየትና ገንዘብ ለመስጠት የተወካዮች ምክር ቤት አባሎችን በዚያው ምክር ቤት አዳራሽ ሰብስባ የነበረ ሲሆን፣ በዕለቱ የክብር እንግዳ እንዲሆንላት ለአፈ ጉባኤው ጥሪ ብታደርግለትም ሳይገኝ በመቅረቱ በሁለቱ ግለሰቦች መካከል ግጭቱ ሊከሰት እንደቻለም ገልፀዋል::

በክረምት ወራት የወያኔ የምክር ቤት አባሎች ወደ ተመረጡበት ቦታ ሄደው ሕብረተሰቡን ያስተምራሉ በሚል ለየእያንዳንዱ የምክር ቤት አባል 3ሺህ ብር እንደሚሰጣቸው የተነገራቸው ቢሆንም ለግማሽ ቀን በተደረገው ውይይት ላይ ተሾመ ቶጋ ባለመገኘቱ የተበሳጨችው አዜብ መስፍን ገንዘቡን አልሰጥም በማለቷ ሽኩቻው እየሰፋ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ተሾመ ይህንን እርምጃ ሊወስድ የቻለው ከዚህ ስብሰባ በፊት በተሰበሳቢዎች ፊት አዋርዳ ያባረረችው በመሆኑ በመበሳጨት ቂም ይዞ እርሱዋ በጠራችው ስብሰባ ባለመገኘት ቁጭቱን በመወጣት ነው ሲሉም ምንጮች አክለው ገልፀዋል::

«ለብሔር ስብጥርና ለኮታ ማሟያ አድርገናችሁ ብትመጡ ጭንቅላታችን ላይ ወጣችሁ» እያለች ስትሳደብ እንደነበረ የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሰውየውም በበኩሉ «በጭንቅላት እንደምንበልጣችሁ ስለምታውቁ ነው የመረጣችሁን እንጂ በሌላ አይደለም» እየተባበሉ ተራ የመንደር አሉባልታ ድረስ መነጋገር መጀመራቸውን የሰሙ አንዳንድ የተቃዋሚ የምክር ቤት አባሎች ወትሮም ቢሆን ስርዓቱን ቢከፍቱት ተልባ ነው ሲሉ ሲያሾፉባቸው እንደነበረም ገልፀዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዙብ መስፍን የተወካዮች ምክር ቤት የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ስትሆን ፣ ከሌላው የምክር በት አባሎች በተለይ እንደልቡዋ ግቢውን እያሽከረከረች የምትገኝ ሲሆን፤የተወካዮች ምክር ቤት ኃላፊ ተብየው ተሾመ ቶጋንም ከዚህ ቀደም እንደልቧ ስታዘው የቆየ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ድፍረት ከየት እንዳመጣ ባይታወቅም ለሴትየዋ ትዕዛዝ አልገዛም በማለቱ የተነሳ ግጭትና ሽኩቻው የተጀመረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ለምክር ቤት አባሎች ክፍያ ይፈፀም በሚልና አልፈጽምም በሚል ጉዳይ ወደ ተካረረ አተካሮ እንዳስገባቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮ የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል::

እርዳታውን ከውጭ ሀገር በሀገሪቱ ሕዝብ ስም በዶላር እየተረከበች በራሷ ስም በግል የባንክ ደብተሯ ውስጥ የምታስገባው አዜብ መስፍን ሰሞኑን የምክር ቤቱን መዘጋት ተከትሎ ለወያኔ አባሎች ይሰጣል የተባለውን ገንዘብ በመከልከሏ የተበሳጨው ተሾመ ቶጋ ለአንድ ቀን ስራ ሳይገባ እንደቀረ ምንጮቹ ገልፀው በዚሁ ሁኔታ ከቀጠለ የተሾመ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ያስቸግራል ሲሉም እነዚሁ ምንጮች ገልፀዋል።

እጅ ከማውጣት ባለፈ አንዳችም ቁም ነገር የማይፈፅሙት የወያኔ የምክር ቤት አባሎች ገንዘቡን አዜብ በማዘግየቷ የተነሳ ተበሳጭተው ሲያማርሯት እንደነበረ የጠቀሱት ምንጮች በተለይም ሰሞኑን ከጣቱ 2:30 እስከ 11:30 ድረስ በየበሩ ላይ ተኮልኩለው ከአሁን አሁን ገንዘቡን ውሰዱ እንባላለን በሚል እዚያው እየዋሉ እንደሚገኙም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ከዚህ ቀደም የወያኔ የምክር ቤት ተጠሪ ሽፈራው ጃርሶ እና ተሾመ ቶጋ በከፍተኛ ደረጃ ተጣልተው እንደበረና በሁለቱ ባለሥልጣናት አለመግባባት የተነሳ የምክር ቤት አባሎች ጭምር ቡድን ፈጥረው የቃላት መለዋወጥ ሲያደርጉ የወያኔው መሪ ሁለቱንም አስጠርቶ ሰድቦ ችግሩን የቀረፈ ቢሆንም የአሁኑ ግን ላም እሳት ወለደች ሆኖበት ሚስቱን የመቆጣትና የመገሰፅ አቅም በማጣቱ ምክንያት ሰውየውን ብቻ ሊያፈጥበት እንደሚችል የገመቱት ምንጮች በሁሉም ስፍራ እኔ ልታይ ልታይ ማለት ያበዛችው አዜብ አሁን እየፈፀመች ያለችውን ተግባር የባሏ ቢጤ አምባገነን መሆኗን የሚያሳይ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል።

በአሁን ወቅት የኑሮ ውድነቱ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ በናረበትና ረሀቡ በየቀኑ ሕዝቡን እየጨረሰ ባለበት ወቅት ለተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ብቻ የደመወዝ ጭማሪ መደረጉን እነዚሁ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

ከሰኔ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረገው ይኸ የደመወዝ ጭማሪ የተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ 300 ብር ምክትል ሰብሳቢ 250 ብር እና የቋሚ ኮሚቴ አባል ላልሆኑት ደግሞ 100 ብር በየወሩ እንዲከፈላቸው መታዘዙን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

የራሳቸውን ሕልውና እንኩዋን ማስከበር ያልቻሉት የወያኔ የምክር ቤት አባሎች በአሁን ሰዓት ለዚያውም በሳምንት ሁለት ቀን ማክሰኞና ሐሙስ ብቻ ተቀምጠው ለሚውሉት የወር ደመወዝ 2700 ብር የሚከፍላቸው ሲሆን፣ የሰሞኑ ድጐማ ደግሞ ኑሮ ተወደደ እኛም ተጐዳን ብለው በቅርቡ ባቀረቡት ጥያቄ የተደረገ የደመወዝ ጭማሪ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

ከደርግ ጊዜ ጀምሮ በግቢው ውስጥ ፅዳትና ሌሎችም ቋሚ የምክር ቤቱ ሰራተኞች የደመወዝ እድገት ሳይሰጣቸው ባሉበት እየረገጡ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ የመዋቅር ማሻሻያ በሚል ወያኔ አመጣሽ መዋቅር በርካታ ሰራተኞችን ለማባረር በዝግጅት ላይ መሆኑን በመስማታቸው የተነሳ ክፉኛ ተደናግጠው እንደሚገኙ የገለፁት ምንጮቹ በአሁን ሰዓት ሁሉም ሠራተኞች በኑሮ ወድነቱ የተነሳ እያማረሩ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል ሲሉ ምንጮቹ ገልፀዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ40 ዓመት በላይ ሲያገለግል የቆየው የከተማ አንበሳ አውቶቡስ የውስጥ መምሪያዎችን ለማፍረስ እና ሰራተኛ ለመቀነስ ጥናት አጠናቅቆ እንደሚገኝ የድርጅቱ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ::

ለብዙ ዓመታት በዚሁ ድርጅት በተለያዩ ሙያዎች ሲያገለግሉ የቆዩት ሠራተኞችን ለማባረር ቢ.ፒ.አር. በሚል አዲስ ወያኔ አመጣሽማባረሪያ ስልት ጥናት ተደርጐ ያለቀ ሲሆን፣ በቅርቡ ተግባራዊ ይሆናል ያሉት ምንጮች በተለይም የተለያዩ መምሪያዎች በውስጡ የነበረው ይኸው ድርጅት መምሪያዎችን የሚፈርስ በመሆኑ ሰራተኛውም እንደሚበተን ስጋታቸውን ገልፀዋል::

ድርጅቱ ሲመሰረት አብረው የጀመሩ ያሉበት መሆኑን የገለፁት ምንጮች በትምህርትና በእድሜ በሚል ሠራተኛውን ለማባረር ጥናቱ ተጠናቅቆ ተግባራዊ ሊደረግ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች እዚህ ድርጅት ውስጥ ሠራተኛ ለመሆን የግድ የወያኔ አባል መሆን ያስፈልጋል ሲሉም ገልፀዋል::

በእውቀትና በችሎታ መመዘኛ የቀረ መሆኑን የገለፁት ምንጮች የወያኔ አባል የሆነ በተለይም ከዚህ ቀደም የነበረ የወያኔ አባል ማንም የማያንቀሳቅሰው ሲሆን፣አባል ያልሆኑት ግን ያለምንም ጥርጥር የመባረር እጣ ፈንታ እንደሚደርሳቸው ምንጮች ገልፀዋል::

በሀገሪቱ ታሪክ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ አንበሳ የከተማና የክፍለ ሀገር አውቶብሶችን አሰማርቶ የሚንቀሳቀስ ድርጅት የነበረ ሲሆን፣ ወያኔ የከተማውን ብቻ ትቶ የክፍለ ሀሩን ገንጥሎና ዋሊያ የአገር አቋራጭ አውቶቡስ በሚል ለሠራተኛው በአክሲዮን ሽያጭ ያከፋፈለ ሲሆን፣ በቅርቡም ይኸው የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ድርጅትም ሳይሸጥ እንደማይቀር ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

በሌላ በኩል የቦሌ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች የድርጅቱን አመራሮች ለመደብደብ ሲያሯሯጧቸው እንደነበረ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 5 ላይ የድርጅቱ ባለስልጣናት ከወያኔ የወረደላቸውን ሠራተኛ ቅነሳ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ተሰባስበው በቢሮ ውስጥ እንዳሉ ሠራተኛው ቀድሞ መረጃ ስለደረሰው ችግሩን ለመነጋገር ሶስት ተወካዮችን ቢልኩም ባለስልጣቱ ባለመቀበላቸው በቁጣ የገነፈሉት የማተሚያ ቤቱ ሰራተኞች በዱላና በድንጋይ እያሯሯጡ ድብደባ ለመፈፀም ቢሞክሩም ሁሉም የወያኔ ሹመኛ ኃላፊዎች ያመለጡ ሲሆን፣ ስራ አስኪያጁ ግን ሽንት ቤት ውስጥ ገብቶ ከውስጥ ቆልፎ በፖሊስ እርዳታ እንደተረፈ ከምንጮቹ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

ለረጅም ዓመታት በዚያው ማተሚያ ቤት ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው ይኸው ግለሰብ መጀመሪያም ወደዚህ ስልጣን ሲመጣ የማተሚያ ቤቱን ሠራተኞች በፖለቲካና በደህንነት ስራ ወጥሮ ይይዛል ተብሎ ታምኖበት መሆኑን የጠቀሰው የደረሰን የምንጮቹ ዘገባ ጉዳዩን ሲያጠናክር ቆይቶ አሁን ሰራተኛውን አባርሮ ለኪሣራ ተደረገ ተብሎ ድርጅቱን ለመሸጥ ከአለቆቹ ከወያኔዎች የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በሠራተኛው ቆራጥ እርምጃ ሁኔታው ለጊዜው የከሸፈ ሲሆን፣ ስራ አስኪያጁ ከዚያን እለት ጀምሮ ልዩ ጥበቃ እየተደረገለት ስራ የሚገባ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልጿል::

ከዚህ በፊት የነፃ ፕሬስ ውጤቶች እንዳይታተሙ ከፍተኛ ጉትጎታ እያደረገ በተለይም ለደህንነት ክፍሉ ሪፖርት ሲያደርግ የነበረ ግለሰብ ነው ያሉት ምንጮቹ በሠራተኛው ላይ የሚያደርሰው ጫናና በደል የተነሳ በርካታ ነባርና ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ሥራቸውን ለቀው እንደወጡም ጨምረው ገልፀዋል።

በአሁን ሰዓትም ከስፖርት ጋዜጣ ውጭ አንድም የግል ጋዜጣ የሚባል አናትምም ብሎ አቋም ወስዶ ያለ ማተሚያ ቤት ቢኖር ቦሌ ማተሚያ ቤት ነው ያሉት ምንጮቹ በፖለቲካው ውስብስብ ስላደረገው ስራውና ፖለቲካው ሊለይ አልቻለም ብለዋል።

የሱማሌ ክልል ፖሊሶችን ማመስ አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገለፀ። ለአንድ ሳምንት ያህል የሱማሌ ክልል ፖሊሶችን በግመገማ ሰበብ ሲመነጥሩ የቆዩት የወያኔ ባለሥልጣናት ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም 68 ፖሊሶችን በማባረር ተጠናቅቋል።

ወያኔ ከዚህ ቀደም በዚያው ክልል ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ከ100 በላይ ፖሊሶችን ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል ያለምንም ማስረጃ ከስራ ያባረረና ገሚሱንም ያሰረ ሲሆን፣አሁንም በተመሳሳይ መልኩ ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ጋር ግንኙነት ፈጥራችኋል በሚል 68 ፖሊሶችን ከስራ ያባረረ ሲሆን፣ 28ቱን ያህል ደግሞ ለእስር እንደዳረጋቸው ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

ወትሮም በሚሰራው ስራ የሚደናገጠው የወያኔ ቡድን በሱማሌ ክልል በሚደርስበት ድንገተኛ ጥቃት የተነሳ በክልሉ የሚሰሩ የፖሊስ አባላትንና ነጋዴዎችን እያሰቃየ ሲሆን፤አሁንም ለአንድ ሳምንት ከአዲስ አበባ በተጓዙ የደህንነት አመራሮች ጋር በተደረገ የመንጥር ግምገማ 68 ከተራ ፖሊስ እስከ ሻለቃ ማዕረግ ያላቸው ፖሊሶችን ከስራ ያባረረ መሆኑን የገለፀው ይኸው የደረሰን ዘገባ 28ቱ ደግሞ ወደ ዘብጥያ መውረዳቸውንም ገልጾዋል:::

ወያኔ እራሱ በፈጠረው ችግር ምክንያት በተለያዩ አቅጣጫዎች ጥቃት እየደረሰበት ሲሆን፣ በተለይም በኦጋዴን ውስጥ በየቀኑ ወታደሮች እየሞቱበት በመሆኑ በጅጅጋ፣ በደገሐቡር፤ በፊቅና በሌሎችም ከተሞች ያሉ የክልሉ ፖሊሶች ለታጣቂው መረጃ በማቀበላቸው ነው ጥቃት የሚደርስብኝ በሚል በክልሉ ፖሊሶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ከማሳደሩ የተነሳ በየጊዜው እያባረረና እያሰረ መሆኑን የገለፀው ዘገባ እስካሁን የተባረሩትና የታሰሩት ፖሊሶች ከ200 በላይ እንደሚሆኑም ጨምረው ገልፀዋል።
ከተራ ፖሊስ እስከ ሻለቃ ድረስ ያሉትን ፖሊሶች ያባረረው የሕወሓት አባሉ አቶ ተወልደ ገ/መድህን የተባለው የትግራይ ተወላጅ ሲሆን፣ ይህንን ተግባር ለፈፀመበት ውለታ የቤት መኪና ተሸልሟል።

ክልሎች እራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ ብሎ ወያኔ ባወጣው ሕገ- መንግስቱላይ ቢያሰፍርም ቃሉና ተግባሩ መቸውንም የማይገናኙ በመሆኑ ለሱማሌ ክልል ፖሊስ ኮሚሽነር ምክትል ኮሚሽነርነት ከትግራይ አምጥቶ የሾመ ሲሆን፣ ይህ የትግራይ ተወላጅና የሕወሓት አባሉ የደህንነት ስራ እየሰራ ሪፖርት ለበላይ አካል እያቀረበ እንደሚገኝም ዘገባው አስረድቷል።

በተለይም የክልሉ ባለሥልጣናት ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ስለሚጠረጠሩ ውሏቸውንና አዳራቸውን እግር በእግር የሚከታተል ግለሰብ ሲሆን፣ ለዚሁ ተግባር እንዲያመቸው በክልሉ ምክትል ኮሚሽነርነት ስልጣን እንደተሰጠው ታውቋል ሲል ዘገባው አብራርቷል፡፡

በክልሉ ውስጥ ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላችሁ እየተባሉ የታሰሩት ዜጐች ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ሲሆን፣ አደገኛ ናቸው የተባሉት ደግሞ ከጅጅጋ እስር ቤት አውጥተው ዝዋይ እስር ቤት እያስገቧቸው ሲሆን፣ በቅርቡ 28 ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በደህንነት ታስረው የነበሩትን እስረኞች በእነ ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማሪያም ላይ የሞት ቅጣት ያስተላለፈው ዳኛ ኑር ሰይድ የተባለው ግለሰብ በዝቅተኛ ዋስ የለቀቃቸው ቢሆንም እስረኞቹ ተለቀው በራፍ ላይ እንደደረሱ ተመልሰው በደህንነቶች ታፍሰው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውን ዘገባው አስረድቷል፡፡

እስረኞቹን በዋስ ለቀሀል የተባለው የወያኔ ካድሬው ዳኛ ኑር ሰይድ የሰራው ስራ ከፍተኛ ጥፋት ነው በመባሉ ከስራው እንዲባረርና በቁም እስረኝነት እንዲቆይ መደረጉን ይኸው የደረሰን ዘገባ አብርቷል፡፡

የወያኔ ቡድን በሱማሌ ክልል ውስጥ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት በመሆኑ ከ4 ክፍለ ጦር በላይ አሰማርቶ የሚገኝ ሲሆን፣ ጦሩም በሕወሓቱ ሜጀር ጄኔራል አብርሃም ገ/እግዚአብሔር እንደሚመራ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የማረሚያ ቤት ፖሊሶች ናቸው የተባሉ መኮንኖች ለስልጠና ወደ አሌልቱ ካምፕ ከሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እንዲገቡ መደረጉ ታወቀ፡፡

የማረሚያ ቤት ምንጮች እንደገለፁት ከሆነ በቅርቡ ያለ አቅማቸው የተሰጣቸውን የመኮንነት ማዕረግ ጋር ለማጣጣም ይረዳ ዘንድ ስልጠና ይሰጣቸው የተባለ ቢሆንም ወያኔ ውስጡ በፈጠረው ፍርሃት የራሴ ናቸው የሚላቸውን ፖሊሶች የካድሬነትና የደህንነት ትምህርት ሊሰጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከምክትል መቶ አለቃ እስከ ሻምበል ማዕረግ የተሰጣቸው እነዚህ የወያኔ መኮንኖች የፖለቲካ ትምህርት ለ3 ወር እንደሚሰጣቸውና እንደሚመረቁ የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ የሚባረር ሊኖር እንደሚችል ምንጮቹ ገልፀዋል፡

ከዝዋይ፣ ከድሬደዋ፣ ከቃሊቲና ከሸዋሮቢት ተውጣጥተው የሚሰለጥኑት መኮንኖች በአሌልቱ ማሰልጠኛ ካምፕ ሲሆን ከሻለቃ በላይ ማዕረግ ያላቸው ደግሞ በኮልፌ ፖሊስ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሕዝቡ በኑሮ ውድነትና በችግር እየተሰቃየ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ የፓርቲዬ ፅህፈት ቤት ያለውን በ130 ሚሊዮን ብር ሊያስገነባ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ፡፡

ወያኔ ሕዝቡ በተራበበት በዚህ ወቅት ለሕዝቡ ቅድሚያ ድጐማ ማድረግ ሲገባው ያለአንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ 130 ሚሊዮን ብር የሚፈጅ ሕንፃ በአራት ኪሎ ፓርላማ ፊት ለፊት ሊያሰራ መሆኑን ምንጮች አጋለጡ።

ወያኔ ባልጠፋ ቢሮ እንደልቡ እየተመነሸነሸበት ባለት በዚህ ወቅት ሕዝቡ ተርቦ የሚቀምሰው አጥቶ በችግር እየተጠበሰ ያለአንዳች ይሉኝታ በ130 ሚሊዮን ብር ወጪ ሕንፃ ሊያስገነባ ሲሆን ይህ ብር ከነጋዴዎች ኪስ የሚመጣ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ሀብታም ነጋዴዎች በስልክና በደብዳቤ ገንዘብ እንዲያዋጡ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ከስር እያስፈራሩ የሚቀበሉ ሰዎችም ተመርጠው አስተባባሪ ተብለው የተሾሙ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል ሚሚ ስብሐቱና ወንድሙዋ መሆናቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በ130 ሚለዮን ብሩ አራት ኪሎ ከፓርላማ ፊት ለፊት የኢህዴግ ፅህፈት ቤት የሚገነባ ሲሆን፣ በሰበታ ከተማ ደግሞ ለካድሬዎች ማሰልጠኛም በተጓዳኝ የሚገነባ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ለዚህ ሕንፃ አላዋጣም የሚል ነጋዴ ቢኖር የሚደርስበት መከራና ስቃ የከፋ መሆኑንም ገልፀልዋል።

የወያኔው አረመኔ ቡድን በሀገሪቱ ግንባር ቀደም ሆነው ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች በእስር ሲያንገላታ ከመቆየቱም በላይ ከጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ከስራ ውጭ ያደረጋቸው ቢሆንም ከ10 ዓመት በፊት በታተመ ጋዜጣ ጋዜጠኞች ላይ እንደ አዲስ ክስ መጀመሩን የማዕከላዊ ምንጮች ገለፁ።

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ በ1990ዓ.ም ጭምር ታትመው የተሰራጩ ጋዜጦች ላይ በሰፈሩ ዘገባዎች በወቅቱ በነበሩ አዘጋጆችና አሳታሚዎች ላይ አቃቤ ሕግ ክስ መስርቶ በማዕከላዊ ምርመራ ቃላቸውን እየሰጡ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

ከ5 ዓመት በፊት የሞቱት ሁሉ ሳይቀር ቃላቸውን እንዲሰጡ እየታደኑ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ከሀገር በወጡትም ላይ ክስ ተመስርቶ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

ብዙነሽ ደበበ የተባለችው ሴት የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኛ ዘጋቢ የተባለ ጋዜጣ አሳታሚና ዋና አዘጋጅ ሆና ስታገለግል የቆየች ሲሆን፤ ጋዜጣው መታተም ካቆመ 8 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን እሷም ከሞተች አምስት አመት እንደሆናት ገልፀው አሁን እንዲህ እንደ አዲስ አዲስ ተከስሳ በፖሊሶች እየተፈለገች መሆኑን ምንጮች ገልፀዋል።

ወያኔ የነፃውን ፕሬስ ስለሚጠላውና ስለሚፈራው በተለይም በአዘጋጆቹ ላይ የእስራት እርምጃ እየወሰደባቸው እያንገላታቸው ሲሆን በዚህም እንግልት የተማረሩ በርካቶቹ ወደ ተለያዩ ሀገራት ተሰድደው የወጡ መሆኑ ይታወቃል በሀገር ውስጥም ያሉት ጥቂቶች ቢሆኑም በነሱም ላይ እንደገና እንደ አዲስ ከ10 ዓመት በፊት በታተሙ ጋዜጦች ተጠያቂ ተደርገው እየታደኑ መሆኑ አስገራሚና አስቂኝ ነው ሲሉም ምንጮች ገልፀዋል።

ታሪክ ፤ገናናው፣ማዕበል፣ ኢትዮ ታይም፣ ዘጋቢ፣ አገሬ የሚባሉና ሌሎችም ጋዜጣ አሳታሚና አዘጋጆች ከ10 ዓመት በፊት በታተሙ ፅሁፎች ተከስሰው እየታደኑ መሆኑ ወያኔ እስከዘሬ ድረስ በጋዜጠኞቹ ላይ የወሰደው እርምጃ ስላላረካው በአደስ መልክ ሊበቀል መነሳቱ አስገራሚ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ቡድን በቅርቡ የሕዝብን ሐሳብ የሚያሰራጩ የራሱን ገመና የሚያጋልጠበትን የነፃ ፕሬስ ጋዜጦችን እንዳይተታም ለማድረግ አዲስ ገዳቢ፣ አፋኝ፣ የፕሬስ ህግ ያፀደቀ ሲሆን፣ ይህንኑ አፋኝ ሕግ በመቃወም በርካታ አለም አቀፍ ድርጅቶች መግለጫ እያወጡ ሲሆን፣ ሰሞኑን ሲፒጄ ለሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ተብየ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ በፊርማቸው ሕጉን እንዳያፀድቁ ደብዳቤ ፅፎላቸዋል፡፡